# ሕዝብን የናቁ ሁሉ አወዳደቃቸው መቸም አያምርም

አምባገነኖች በዕብሪት ሲወጠሩና ማንም አይነቀንቀንም በሚል ሲዘባነኑ ሕዝብን በጣም ይንቃሉ። በሀብታቸውና በሀይላቸው ይመካሉ። ሰፊው ሕዝብን አፍነውና ቀይደው ለዘለዓለ ም የሚገዙት ይመስላቸዋል። ከገዢዎች ባሻገር ደግሞ ሌሎች ተማርን አወቅን ባዮች፤ በለስ የቀናቸው የመሰላቸው ዘፋኞች፤ ምሁራን፤ ጡረታ የወጡ አዛውንቶች ወዘተም በበኩላቸው ሕዝብን ይንቁና ሳይመርጣቸው መሪዎችህ ነን ብለው ሲቯቯሙበትም ማየት ተገደናል። ፖለቲካ ለምርጦች ብቻ የተመደበ ባይሆንም አላፊው አግዳሚው የፖለቲካ መሪና የሕዝብ አለቃ ነኝ ብሎ ሊሰየም ሲነሳ አሳዛኝ ደረጃ የደረሰ የሕዝብ ንቀት መሆኑንም ማስረዳት የግድ ይሆናል።

ይህ ችግር የኢትዮጵያ ብቻ አይደለም። በአውሮጳ በእግር ኳስ ጨዋታ ዝናን ያተረፉ አፍሪ ካውያን የየሀገራቸው መሪ ሊሆኑ ሲሞክሩ አይተናል። የራሳችንም አንድ ዝነኛ ሯጭ ስለ ፖለቲካ ለ ን ሳይሆን ሀ ን ገና ሳይረዳ የኢትዮጵያ ፕሬዚዳንት ልሆን እችላለሁ ብሎ የለፈፈ ውንም ማስታወስ እንችላለን። አፄ ኃይለሥላሴ ሕዝብ ሕፃን ነው፤ የሚበጀውንም አያውቅ ሲሉ ምናልባትም ሥዩመ መለኮት ነኝ ከሚሉት ዕምነታቸው ጋር የተያያዘ ነው ብሎ መረዳ ት ይቻል ይሆናል። ዛሬ ለዴሞክራሲ ቆመናል የሚሉ ቀልደኞች ለአፄው ሀውልት ካልተሰራ ሲሉ አፄውና ስርዓታቸው በሕዝብ ላይ ስላደረሱት ጉዳቶ ከቶም ማንሳት ተስኗቸዋል፤አቅዋ ማቸውም ማፈሪያዎች አድርጎ በአደባባይ ያሳጣቸዋል። እነ በላይ ዘለቀንና ስንቱን አርበኛ ማን ገደለ? እነ መንግስቱና ገርማሜ ንዋይን ወዘተ ማን ሰቀለ? ጥላሁን ግዛውን ማን አስገደለ ? የደራሳን፤ ባሌንና ጎጃምን አርሶ አደር ማን ጨፈጨፈ ? የኤርትራን ችግር ማን ቀፈቀፈ ? ሚሊዮኖችን አርሶ አደሮችን በጢሰኝነትና ገባርነት ማን መከራ አሳየ? ይህን ሁሉ ግፍ ሰርዞ ኃይሌ ኃይሌ ብሎ መዝፈንና መጮህ በሕዝብ ላይ መቀለድ ነው። መንግስቱ ኃይለማርያም የተባለው አረመኔ ደግሞ በስልጣን ተኩራርቶና ሕዝብንም ንቆ ራሱን ታላቁ ሊቀ መንበር ብሎ ሰይሞ ሕዝብን በሽብር ፈጅቷል። ከኔ በላይ አዋቂ ላፈር ብሎ ሲደነፋም የናቀው ሕዝብ የደም ዋጋ ከፍሎ ጥሎታል። ዛሬ በስልጣን ላይ ያለው ደግሞ የሕዝብን ትግል ሰርዞ በኔ ትግል፤ በኔ ዘሮች ትግል ብቻ የደርጉ ስርዓት ወደቀ ብሎ ሲመፃደቅ ተደም ጧል። ከወርቅ ዘር የመጣሁ ነኝና ሌሎቸ ሁሉ መዳብ ሊባሉም አይቻልም በሚል ይህ አሰቃ ቂ ዘረኛ ስርዓቱን አስፍኖ እነሆ ሀያ ዓመትን ደፍኗል። ወያኔ ሕዝብን ይንቃል--ማንም አይነ ሳብኝም፤ ቢነሳብኝም በፍጅት አሳቅቄ ፀጥ አረገዋለሁ ብሎ ያምናል። ተቃዋሚዎችን አንድ ም በሆዳቸው አሊያም በፍርሀታቸው አንበረክካለሁ ያለውም የንቀት ድምዳሜው ከሞላ ጎደ ል ሰርቶለታል። ይህም ንቀቱን ይበልጥ አዳብሮለታል ማለትም ይቻላል።

የገዢዎች ጥጋብና ንቀት እንዳለ ሆኖ ለሕዝብ ቆምን የሚሉትም በሕዝብ ላይ ንቀታቸው
ለከትና መረን እያጣ መጥቷል:: ራሳቸውን ምርጥና ልሂቅ ብለውና ሰፊውን ሕዝብ ናቅ
አድርገው በራሱ ላይ በጫንቃው ላይ ሊወዘፉ ራሳቸውን አጭተውና አመቻችተው እንዳሉም
እየታዘብን ነው:: ሩጫ እችላለሁና ልግዛችሁ እንዳለን ዕብሪተኛ ሁሉ ምሁሮች ነበርን፤ ዘፋ
ኝ የመድረክ ሰው ነነ ፤ ቲያትረኛ ነን፤ ዶክተር ፐሮፌሰር ነበርን/ነን፤ ወዘተ እያሉና ለሀገር
ሲታገሉ የቆዩትንና ተመክሮ ያካበቱትን ሁሉ እየሰደቡና እያዋረዱ ከእኛም በላይ መሪና
አዋቂ ለአሳር ብለው መድረክ የሚያጣብቡ በርክተዋል:: በዚህም መንጋ መሀል የወያኔና የሻ
ዕቢያ፤ የአሜሪካና የባዕድ ቅጥረኞች አመቺ ሜዳ አገኘን ብለው መፈንጨታቸውን እያየን
ነው:: ዛሬ በአሜሪካ ምድር ለምሳሌና በኢትዮጵያም በርካታ ኢትዮጵያውያን በአሜሪካ
ተቀጥረው በወገኖቻቸው ላይ በስለላ መሰማራታቸውን ለማወቅ ተችሏል:: ዘመኑ ንፉግ ነው
ብሏል አንድ ኢትዮጵያዊ--ወኔም ጠፍቷል፤ ሀገር ፍቅርም ተኗል፤ ሰብዕናን ማክበር ማስከበ
ርም ባዕድ ሆኗል:: ፍርሀት ማንነትን ሰርዟል::ታሪካችን ወያኔ ሊል እንደሚቃጣው በተረትና
ተረት ሊፈረጅ በቅቷል:: መደህየት በሀብት ብቻ ሳይሆንም መንፈስና ሞራልንም ጠቅልሎ
ይገኛል:: አዔው ሕዝብን ንቀው ሕዝብ ምንም የማያወቅ ሕፃን ነው ሲሉ፤ መንግስቱም ይህን
ኑ ተቀብሎ ደግሞ የማላውቀው ሳይንስ ገና አልተፈጠረም አልተገኘም ሲል የዘንድሮው
ጮሌ ደግሞ ወዲ ትግራይ እንተሎ ከቶስ ማነው ሌላ ምሁር አዋቂ የሚባለው ብሎ የሚያቅ
ራራ ነው:: የሕዝብ ጎራ መሪና አሸከርካሪ ነን ብለው የተሰየሙትን ግለሰቦች ይዘትና ተመክ
ሮ፤ ችሎታና ፅናት፤ ወኔና ቆራጥነት ስናይ ምናልባትም ዘረኛው መንጋ በላያችን ላይ ይከር
ም ይሆን ብለን መስጋታችን ስህተት አይሆንም:: ትላንት በሽብር ወንጀል የተሳተፉ ወይም
ሕዝብ ሲፈጅ ዝምታን የመረጡ ፤ ትላንት ለአረመኔ የዘፈኑና ካድሬ የነበሩ፤ በቅርብ ጊዜ
ለወያኔ አድረው ወይነው ሕዝብና ሀገርን የጎዱ፤ የሕዝብን ቅንጅትና ህብረት ያፋለሱ፤ ዛሬም
ቢሆን ከወያኔ ጋር ከቶም ያልተቆራረጡ፤ የመጀመሪያ ፍቅራቸው ለሀገር ሳይሆን ለቀጣሪያ
ቸው ሆኖ ሀገርን የከዱ ሁሉ በተዓምር የሕዝቡን ወገን መቀላቀል ሳይሆን እንምራ ባዮች
ሆነው ሲገኙ ምንኛ ሕዝብን እንደናቁ የሚያሳይ ነው:: ክቡርና ታላቅ የሆነው የኢትዮጵያ
ሕዝብ ዕውቀትን ሳይሆን ገንዘብን ባካበተ ሯጭ፤ ችሎታ አልባ በሆነ ሻለቃና መጋቢ ሀምሳ
አለቃ፤ ጡረታ በወጣ ምሁር ፤ ወኔ ቢስነቱን ባስመሰከረ ልሂቅ በሉኝ ባይ፤ በከሀዲና ባንዳ፤
በአንጃና በታኝ፤ በባዕድ ቅጥረኛ ከቶም መቼም የሚገዛ አይደለም:: ካልተጨፈጨፈ በስተቀ
ር፤ ጭቆና ካልሰፈነበት በቀር :: ይህ ደግሞ ያለፈውን ግፍ መቀጠልና ሀገርን ማሰቃየት ነው
:: ሕዝብን መናቅ ነው::

የቀድሞዎቹ ሲተርቱ የተናቀ ያስረግዛል ይላሉ፡፡ ትምህርት አዘል ጥቅስ ነው፡፡ የተናቀ ሕዝብ ዙፋን ይገለብጣል--የጊዜ ጉዳይ ብቻ ነው፡፡ ሕዝብን ንቀው በሕዝብ ላይ በዚህም በዚያም ሊፈነጩ የሚቃጡ ሁሉ ውሎ አድሮ ምሳቸው ውድቀት ነው፡፡ መለስ ዜናዊ ፖሊሶ ችህ ለምን ወደ ሰው ሳይሆን ሰልፍን ለመበተን ወደ ሰማይ አይተኩስም ቢባል ጠባችን ከአሞራዎች አይደለም ብሎ መለሰ የተባለው በቀልድ ደረጃ ብቻ የሚወሰድ አይደለም ፡፡ የዚህን ቡከንና ግብዝ ፍጡር ንቀት ያመለክታል፡፡ ሕዝብ ሲፈጅ ሲረገጥ ሊቃወሙ ቀርቶ በለሆሳሰም ቢሆን ትንፍሽ ያላሉ፤ ምቾታቸውንና ኑሮአቸውን ሲገፉ ቆይተው ጡረታ ሲወጡ ወይም በዚህም በዚያም ከነበሩበት ስምሪት ሲፈናቀሉ ወደ ፖለቲካ መጣን ገባን ብቻ ማለት ሳይሆን መሪያችሁ ነን፤ ሽግግር እናዘጋጅላችኋለን ወዘተ ብለው በትዕቢትና በሕዝብ ንቀት ሲጮሁ ዛሬም እያየን ነው፡፡ ያሳዝናል!

ዋናው ጉዳይ መለስ ዜናዊና ግብረአበሮቹን ሕዝብን መናቅ ከባድ ስህተት መሆኑን ሕዝብ ሊያሳያቸው አስፈላጊና ወቅታዊ መሆኑ ነው፡፡ ሀይል የሕዝብ ነው--ሕዝብም በሀይሉ መጠቀ ም በሚችልበት ጊዜ የናቁት ሁሉ ያፍራሉ፤ ተገቢ ቅጣታቸውንም ይቀበላሉ፡፡ የመለስ አገዛ ዝም ይወድቃል፤ይንኮታኮታል፡፡ ያኔም በእውን ማን እንደሚሆን አቸናፊ ለሁሉም ግልፅ ይሆናል፡፡